# እህ ዛዲያማ!

በአንድ ጎጆ
እህ ዛዲያማ!
አንድ ቁርንጮ ይነጠፍና፣
ምርጫ በይፋ ይታወጅና

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! ምን ልንገራችሁ፣
የደረሰውን ታውቂታላችሁ

ሕዝብ ጨብጦ ሙሉ ነፃነት፣
ያገር የመንግሥት ባለቤትነት፣
መያዝ ካልቻለ በነፃ ምርጫ፣
መቅመሱ አይቀርም እንደኛ ጡጫ

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! ምን ልንገራችሁ፣
ያፍሪካን ምርጫ ታውቂታላችሁ

እዛ ኬንያ ጎረቤት ሀገር፣
በምርጫ ሰሞን አንዱ ሲናገር
ይሄ ፈጽሞ ኢትዮጵያ አይደለም፣
የህዝባችን ድምፅ ተሰርቆ አይቀርም
እንዳለው ሁሉ ህዝቡ በአንድነት
አርበድብዶታል ያለውን መንግሥት

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! ምን  ልንገራችሁ፣
የኛንም ጉዳይ ታውቂታላችሁ

እዛም ዚምባብዌ ምርጫ ተደርጎ፣
ድምፅ የሰጠውን ህዝብ ፈልጎ፣
ቆጠራ አጣርተው ባለመናገር፣
አፍነው ይዘው ፈጥረዋል ሽብር

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! ምን ልንገራችሁ፣
ያፍሪካን ምርጫ ታውቂታላችሁ

ሌላም ጉድ አለ ሰሞኑን በግብጽ፣
ተቀናቃኙን በታቀበ ድምፅ፣
አፍኖ ይዞ እሱው ሊመረጥ!
ከረመ ገዢው መግለጫ ሲሰጥ
ይሄ ግልጽ ነው ካጀማመሩ፣
የህዝቡ ምርጫ ጠቧል ድንበሩ

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! ምን ልንገራችሁ፣
የኛን ሃገርም ታውቂታላችሁ

የአፍሪካ ምርጫ ካውሮፓዎች ጋር፣
የአፍሪካ ምርጫ ካሜሪካ ጋር፣
ምኑም አይገጥምም በባህል በዘር
የማስመሰያው ያፍሪካ ምርጫ፣
እያጋደለ ህዝብ እያንጫጫ፣
እስካሁን ዘልቋል አጥቶ መቋጫ

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! በአንድ ጎጆ
እህ ዛዲያማ! እህ ዛዲያማ!
አንድ ቁርንጮ ይነጠፍና
ምርጫ በይፋ ይታወጅና

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! ምን ልንገራችሁ፣
የኛንም ጉዳይ ታውቂታላችሁ

ህዝብ ጨብጦ ሙሉ ነፃነት፣
የሀገር የመንግሥት ባለቤትነት
መያዝ ካልቻለ በነፃ ምርጫ፣
መቅመሱ አይቀርም የገዢ ጡጫ

እህ ዛዲያማ!
እህ ዛዲያማ! ምን ልንገራችሁ
የአፍሪካን ምርጫ ታውቂታላችሁ።

ከወለላዬ

ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም. - ስዊድን
**April 21, 2008 - SWEDEN**